

# ፍትሃዊነት ለሁሉም

2025

የአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች

## ስትራቴጂካዊ እቅድ 2020-2025

ACPS
Alexandria City Public Schools

# የእኛ እይታ፤

በብዝሃነት ባለው እና ተለዋዋጭ በሆነው አለም ሁሉም ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማስቻል።

# ተልእኮ፤

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ተማሪዎችን በማነሳሳት ውጤታማ መሆናቸውን ያረጋግጣል። እንዲሁም ለትምህርት እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን መፍትሄ ያፈላልጋል።

# የእኛ ዋና እምነቶች፤

በምናከናውናቸው ስራዎች በሙሉ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የትምህርት ህብረተሰብ እነዚህ ዋነኛ እምነቶችን መከተሉን ያረጋግጣል። እኛ…

- አስተናጋጅና ተቀባዬች፣
- ምቹ ሁኔታ ኋይል ፈጣሪዎች፣
- ፍትሃዊነት ላይ የምናተኩር፣
- አዲስ ነገር ፈጣሪዎች፣
- ውጤት ላይ የምናተኩር ነን።

# ግልፅ ነው። ድፍረት አለው። ስለፍትሃዊነት እና ምቹ ሁኔታ ስለመፍጠር እና ተማሪዎችን የበለጠ እንዲያከናውኑ ማነቃቃትን ይመለከታል።

የአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች ቦርድ በጁን 2020 ለአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች ፍትሃዊነት ለሁሉም 2025 የሚል ስትራቴጂካዊ እቅድ አፅድቅል።

ፍትሃዊነት ለሁሉም 2025 የስትራቴጂክ እቅድ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ የሚያጠነጥነው በዘር እኩልነት ላይ ይሆናል። የእኛ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ትምህርት ተሳታፊ እንዲሆኑ እና ትምህርት አቀባበል የተሻለ ለማድረግ የትምህርት መማሪያ አስፈላጊ እቃዋችን ማግኘታቸውን እንድናረጋግጥ ይጠይቀናል። የእኛ ትምህርት ቤቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ፣ በጥሩ እና በመልካም ሁኔታ ሁሉንም ለማስተናገድ የተዘጋጁ መሆናቸውን ያረጋግጣል። በትምህርት አስተዳደር ዲቪዝኑ በመላ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮችን መለየት እና ፕሮግራሞች የእድል ማግኘት እና የአስፈፃፀም ልዩነት ማጥበብ እንዲሁም ሁሉም ተማሪዎች ለኮሌጅ፣ ለሙያ ስራ እና ለህይወት ዝግጁ ሁነው እንዲመረቁ ማስቻል። እይታው ትልቅ እና ጎልህ ነው እና ያለው አቅም ግዙፍ ነው።

ፍትሃዊነት ለሁሉም 2025 አምስት ዋና ስትራቴጂካዊ ግቦች አሉት። እነዚህ ስትራቴጂካዊ ግቦችን ለማሳካት የሚደረገው ጉዞ በተጠናከረ መመዘኛ መስፈርት ይለካል። እነዚህ ግቦች በጣም ትልቅ ሙከራ ናቸው። ሆኖም ተስፋ የምናደርገው የእኛ ውጤታማነት በአርአያነት በመላው አገሪቱ የከተማ ትምህርት ቤቶች እንደምሳሌ ይሆናል ብለን እናምናለን።

በጥድፊያ ነው የምንቀሳቀሰው እና አሁን ግዜው ቀጣዩን ትውልድ ማስተማር እንደሆነ እናውቃለን። እንዲሁም ግባችን በትክክል ተግባራዊ መሆኑን ለማረጋገጥ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ያለ ምንም ይሉኝታ ከሁሉም ሰራተኞች፣ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ከፍተኛ ደረጃ እንጠብቃለን። ለኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ወደፊት ለመቀጠል ውጤታማነት ብቸኛው አማራጭ ነው ። ከዚህ ወዲያ ምንም ዓይነት ሌሎች ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዬች ቢኖሩም የእኛ ወጣቶች ምንግዜም የስራችን፣ የውሳኔ መስጫችን፣ የተልእኮችን ማእከሎች ይሆናሉ።

የተለያየ የህብረተሰብ የሚገኝበት የከተማ እና የአካባቢ የትምህርት ቤት አስተዳደር በመሆናችን ብዙውን ግዜ ልዩ የሆኑ እድሎችና የተወሳሰቡ ችግሮችን ፈተናዎች ያጋጥሙናል። ፍትሃዊነት ለሁሉም 2025 ቃል የሚገባው በዚህ ብዝሃነት ባለው እና ተለዋዋጭ በሆነው ዓለም ሁሉንም ተማሪዎች አቅም በመገንባት የሚያልሙትን እንዲያገኙ እና የራሳቸው ግቦች እንዲያሳኩ ማስቻል ነው።

ተፈላጊውን የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዬች፣ የሚያተኩሩባቸው ነገሮች እና ፕሮግራሞች እንቅፋቶችን በማስወገድ የኑሮ ሁኔታ ያሉበት ሁኔታ ተፅእኖ ሳያሳድር የእኛ ወጣቶችን ለማገዝ የሚያስችል እርምጃዎችን እንወስዳለን። ይህም በመላው የትምህርት አስተዳደር ዲሽዝኑ በአስተሳሰብ ረገድ ከቀድሞው የተለየ የአትኩሮት አቅጣጫ ለውጥ ይኖራል። ይህም የሰው ሃይል አመዳደብ፣ ገንዘብ እና የትምህርት አጋዥ ሪሶዋርሶች እና የስትራቴጂካዊ አካሄድ ለውጥ ማካሄድን ያካትታል። ሁሉም ተማሪዎች በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የትምህርት አሰጣጥ ተሳትፎ ማድረጋቸው ለማረጋገጥ ይህም ብዝሃነት እና ተለዋዋጭ በሆነው ዓለም ውጤታማ መሆን እንዲችሉ ያስችላቸዋል።

እኛ ይህንን ስራ ብቻችን ልንሰራው አንችልም። ፍትሃዊነት ለሁሉም 2025 የአንድ ትልቅ ስትራቴጂክ እይታ አካል ነው። በእኛ ከተማ እና ከተለያዩ የከተማው ድርጅቶችን ጋር በተቀናጀ ሁኔታ ልጆችንና ቤተሰቦችን በመደገፍ ተሳትፎ ያደርጋሉ። እነዚህ ተቋማት የአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት ጨምሮ፣ Partnership for a Healthier Alexandria እና የአሌክሳንደሪያ ከተማ የኮሚዩኒቲ እና የሰብአዊ አገልግሎቶች ዲፓርሜንት — የህፃናንት እና የወጣቶችን ጉዳይ ማስተር ፕላን የማዘጋጀት ኋላፊነት ያለበት — ቅንጅት ለመፍጠር በመጀመሪያው በተቀናጀ የአምስት ዓመት የእቅድ አወጣጥ ሂደት መላው የአሌክሳንደሪያ ከተማ አቅም የመፍጠር ስራ ተሳታፊ ሆናል።

ሁሉንም ተማሪዎቻችን አቅም ለመገንባት፣ ለማገዝ በኮሌጅም ሆነ በሚመርጡት የሙያ ዘርፍ እንዲጠናከሩ እና እንዲለወጡ ለማድረግ ፍትሃዊነት ለሁሉም 2025 እቅድ እውን ለማድረግ በሚደረግ ጥረት ከእኛ ጋር ይሁኑ።

ለ2025 አምስት ይስጡን።

# ከስትራቴጂካዊ እቅዱ ጀርባ ያለ ታሪክ።

ይህ የስትራቴጂክ እቅድ የፀደቀበት ዓመት የፓርከር-ግሬይ ትምህርት ቤት የ100ኛ መታሰቢያ ዓመት - በአሌክሳንደሪያ የመጀመሪያዎቹ የአፍሪካ አሜሪካዊያን የህዝብ ትምህርት ቤቶች አንዱ ነበር። የፓርከር-ግሬይ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለመማር የሚያስፈልጋቸው ምንም ነገር አልነበራቸውም። በእርግጥ የትምህርት ቤት መፅሀፍት፣ ቾክ ወይም የቾክ ቦርድ ሰሌዳ ካገኙ እድለኞች ነበሩ። የኮሚዮኒቲ አባላት ወንበርና እና መሰረታዊ የሆኑ የመማሪያ እቃዎችን አበርክተዋል እና ማንኛውም አፍሪካ አሜሪካዊ ተማሪ ትምህርቱን ከስምንተኛ ክፍል አልፎ መቀጠል የሚፈልግ ወደ ዋሽንግተ ዲ.ሲ. በእግር መጎዝ ነበረበት ወይም አውቶብስ ለማግኘት እና ወደ ቤት ለመመለስ ቢያንስ 21 ብሎክ በእግር መጎዝ ነበረበት ።

አሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች በድጋሚ በ1950ዎቹ ፣ 60ዎቹ እና በ70ዎቹ አመታት በግንባር ቀደምት ነበር። ሆኖም በዚህ ግዜ የትምህርት ቤቶችን የዘር ልዩነት ማስቀረትን በመቃወም ነበር። የአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች ታሪክ ረዥም፣ የተወሳሰበ እና ለየት ያለ ነው። የእኛ ታሪክ ችግርን፣ ዘረኝነት፣ ጥላቻንና ግዴለሽነት የተጋፈጠ የኮሚዩኒቲ ታሪክ ነው። የተለያየ እንቅፋት የነበረባቸው ቢሆንም ብዙዎቹ ለፍትሃዊነት እና የሲቪል መብቶች ተከራካሪ ሆነዋል። ለእኛ ያሳላፉት ታሪክ ቅርስ ዛሬ ልናሳካው የምንሞክረው ጉዳይ ነው።

በእርግጥ የእነሱን ታሪክ እኛ ማስቀጠል ኋላፊነታችን ይሆናል። በማንኛውም ተማሪ ላይ ተስፋ መቁረጥ አይኖርብንም እና ፍትሃዊ ለሆነ ትምህርት መታገል መቀጠል ይኖርብናል የማናቸውም ዘር፣ የማህበራዊ የኢኮኖሚ ሁኔታ፣ የሚኖርበት ዚፕ ኮድ፣ የቤተሰብ ሁኔታ እና / ወይም የትምህርት ችሎታ ቢኖራቸውም።

የስትራቴጂክ እቅዱ የእኛ ግብ  ፍትሃዊነት በእኛ ህብረተሰብ ምሶሶ እንዲሆን ማድረግ ነው።  ያን ለማድረግ እኛ የዘር እኩልነት አለመኖርን መቀበል  እና በከተማችን ያለውን ታሪክ ለእዚህ አሁን ያሉ ወጣቶች ያጋጠማቸውን ሁኔታ እንቅፋት አስተዋፆ ያደረጉትን መረዳት ይኖርብናል ።

ዛሬ ብዙ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ከተለያዩ አገራት የመጡ ተማሪዎችን እናስተናግዳለን።  በትክክል 119 አገራት ውክልና አላቸው እና 120 ቋንቋዎች በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ይነገራል።  እኛ ብዝሃነትን እኛ አክብረናል ። ሆኖም ግን ለፍትሃዊነት የምናደርገው ጀግንነት የተሞላበት ትግል ገና አልተጠናቀቀም። ወደፊት ለመግፋት የዘመኑ ልዩነት አሁንም እንዳለ መረዳት ይኖርብናል እና የእኛ ስራ ገና አልተጠናቀቀም።

ይህ የእኩልነት ፍትሃዊነት ምሶሶ ለመገንባት ድፍረት ሊኖረን ይገባል እና ከእኛ ለየት ባሉት ስም ያለምንም ማመንታት መናገር ከጎን መቆም ይኖርብናል።  ለእኛ ወጣቶች እና በእኛ ኮሚዩኒቲ ውስጥ ድምፅ ለሌላቸው እንዲሁም ሁሉም የእኛ ወጣቶች ሊሆኑ የሚችሉትን የሚችሉትን እንዳይሆኑ እንቅፋት የሚሆንባቸውን ለመነቃቀል ጥብቅና መቆም ይኖርብናል ።  ከዚህም የበለጠው ጉዳይ  እያንዳንዱ ልጅ ከፍተኛ ጥራት ባለው የትምህርት ልምድ ተሳታፊ እንዲሆን /እንድትሆን በመማሪያ ክፍል ውስጥ እና ከዚያም ውጭ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የማህበራዊ፣ የስሜት እና የአካዳሚ ፍላጎታቸውን ለማሟላት አንድ ላይ መቆም እና በትብብር መስራት ይኖርብናል።

ይህ  ታሪካችን ነው ለሁላችንም ተማሪዎች፤ ለአሁኖች፣ ለቀድሞዋቹ  እና ለወደፊቶቹም ሲባል ማሳካት የሚኖርብን ኋላፊነት ይሆናል። እኛ ቲይታንስን ሁልግዜም ማስታወስ ይኖርብናል።

# ፍትሃዊነት ለሁሉም 2025 እንዴት የለውጥ ኋይል ይሆናል

## በመረጃ  የሚመራ ይሆናል

የስትራቴጂክ እቅድ ኮሚቴ በወርክቡክ መልክ የተደራጀ አጠቃላይ መረጃ ላይ በመመስረት በመስራት የትኛው የሚሰራ መሆን እና የትኛው ደግሞ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በፍትሃዊነት መነፀር የበለጠ ማደግ ይኖርበታል የሚለውን ለማወቅ ሲመረምር ቆይቶል።   ሂደቱ በመረጃ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ የስትራቴጂክ እቅዱ በተግባር ላይ የተመሰረተ መሆኑን ያረጋግጣል።  የእኛ ስትራቴጂክ እቅድ ምኞት ከመሆን ባሻግር በተማሪዎች ውጤት በቅድሚያ መልካም ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

## አነስ ያለ ግን ብዙ

ፍትሃዊነት ለሁሉም 2025 ቀድሞ ከነበረው የስራቴጂክ እቅድ ጋር ሲነፃፀር ጥቂት ግቦች፣ መስፈርቶች እና ተግባራት ናቸው ያሉት። የሚያተኩረው ቀጣይነት ባለው መንገድ ለውጥ ለማስቀጠል በጣም ወሳኝ በሆኑ ነገሮች ላይ ነው።  ሁሉንም ነገሮች እንደተገኘ ለመስራት ከመሞከር ይልቅ በቅድሚያ መሻሻል በሚገባቸው ጉዳዬች ላይ ነው ያተኮረው - እነርሱን በሚገባ መሰራታቸውን በማረጋገጥ።

## የጋራ የእቅድ ዝግጅት ሂደት

በ2019 የከተማ እቅድ የመከለሻ ግዜ ሲገጣጠም አንድ አጋጣሚ ራሱ ተከሰተ - የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ስትራቴጂክ እቅድ፣ የአሌክሳንደሪያ የኮሚዩኒቲ እና የሰብአዊ አገልግሎቶች ዲፓርሜንት፣ የአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት  እና  ጤናማ አሌክሳንደሪያ ትብብር የአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት የማሻሻያ እቅድ ።  እነዚህ ተቆማት በጋራ አንድ ወጥነት ያለው የእቅድ ዝግጅት ቡድን ፈጠሩ በጋራ እቅድ ለማዘጋጀት፣ በጋራ የማህበረሰብ ተሳትፎ ለማሳደግ ፣ አስፈላጊ መረጃዋችን ለመለዋወጥ እና በጋራ ውጤቶች ላይ ለማተኮር። እነዚህ እቅዶች በጋራ በሚደረጉ የትብብር የዘር እኩልነት እንቅስቃሴዎች፣ የችግር መፍትሄ የሚያስገኝ አገልግሎት በመስጠት እና ልማታዊ የሆነ አቀራረብ በመከተል በስራ ይውላሉ።

### የሰራተኛ  ሃሳብ

እያንዳንዱ ትምህርት ቤት በስራትራቴጂክ እቅድ ዝግጅት ላይ ቢያንስ በአንድ ሰራተኛ ተወክሎ ነበር ።  ይህ ሆን ተብሎ የተከናወነ ጥረት ነበር በእኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉትን የእኛ ተማሪዎች በየቀኑ ተፅእኖ የሚፈጥሩ ለመገንዘብ ያላቸውን እውቀቶችና ልምዶችን ለመጠቀም።  የእኛ ሰራተኞች በትክክል ብዙ የእለት ልጆች ህይወት ላይ ለውጥ ለማምጣት ትልቅ አቅም  እንዳላቸው እኛ እናምናለን።

### አትኩሮት እና ቅድሚያ አሰጣጥ

ፍትሃዊነት ለሁሉም 2025 ሁላችንም ፍትሃዊነት አትኩሮት እና ቅድሚያ እንድንሰጥ ያበረታታናል።  ግቦች፣ መስፈርት፣ ስትራቴጂ እና የተመረጡ ተግባራት መረዳት የሚቻል፣ ሊከናወኑ የሚችሉ እና የወደፊትን ፍላጎት የሚያሳዪ ናቸው።

ለተጨማሪ መረጃ እባክዎን የሚከተለውን ይመልከቱ፤ www.acps.k12.va.us/2025

# ፍትሃዊነት ለሁሉም 2025 እንዴት ነው የተዘጋጀው

በቀድሞ የስትራቴጂክ እቅድ (2015-20) ወቅት የትኛው የሚሰራ እንደሆነ እና የትኛው የበለጠ መሻሻል እንደሚኖርበት ብዙ ነገሮች ተምረናል።  በተመረጠ ቡድን የጥናት ማካሄድ፣ የሰራተኞች አስተያየት ማዳመጥ ስብሰባ፣ የክፍል ምልከታ፣ የተሰባሰበ መጠይቅ ትንተና እና አሁን ያልንን የአካዳሚ ለውጥ ለመገምገም የተሳባሰቡ መረጃዎችን መመርመር ስራ ተካሂዶል።

የስትራቴጂክ እቅድ ረቂቅ የተዘጋጀው ከ60 በላይ አባላት ባለው ከኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሰራተኞች፣ አመራር ፣ ወላጆች፣ የትምህርት ቤት ቦርድ አባላት፣ ከከተማው እና የኮሚዪኒት ተቆማት የተወከሉ የስትራቴጂክ እቅድ ኮሚቴ ነበር። ኮሚቴው ከ2019 መጨረሻ ጀምሮ እስከ ጃንዋሪ 2020 ድረስ በየወሩ ይገናኝ ነበር። በአማካሪዎች FourPoint Education Partners  ከእነርሱ ጋር አብረው የስትራቴጂክ እቅዱ አካል እና ረቂቅ ሃሳብ በማዘጋጀት ይታገዙ ነበር።     ይህ ረቂቅ እቅድ ከዚያም ተጨማሪ አስተያየት ከርእሰ መምህራን ፣ ከኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. አመራር፣ ሰራተኞች እና ከኮሚቴው ከራሱ ሃሳብ ካሰባሰበ በኋላ የመጨረሻው ረቂቅ አዘጋጅቶል። የመጨረሻው የስትራቴጂክ እቅድ ረቂቅ ለትምህርት ቤት ቦርዱ በሜይ 2020 ለአስተያየት ከቀረበ በኋላ እና ከሜይ 2020 እስከ ጁን 2020 ድረስ ለህዝብ አስተያየት ክፍት ሆኖ ነበር።  የሁሉም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አስተያየት ከተሰባሰበ በኋላ የመጨረሻው የስትራቴጂክ እቅድ በትምህርት ቤት ቦርዱ ቦርዱ በጁን 26፣ 2020 ፀድቆል።

# የዘር እኩልነት ዋነኛው ጉዳይ

የአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የዘር እኩልነት ቃል ይገባል።  የዘር እኩልነት ማለት የአንድ ሰው ህይወት፣ እድል ማግኘት እና ውጤት ዘር የማይወስነው መሆን ሲረጋገጥ ነው።

የዘር እኩልነት አለመኖር ጉዳይ በትምህርት ቤታችን ስርዓት የተፈጠር እና የሰረፀ  መሆኑን በመረዳት ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የሚከናወኑ ተግባራት የዘር እኩልነት በማእከልነት የሚያገለግል ዋነኛው ጉዳይ ነው።  በጣም በዘር ልዪነት ዙሪያ የተደራጀ ስርዓት ዋጋ የሚያስከፍል ነው እና ዝቅተኛ ውጤት ነው የሚኖረው እና ለሁሉም ቡድኖች የህይወት እድል አነስተኛ ነው የሚሆነው።  በዘር እኩልነት ላይ ማተኮር ግቦችን እና ስትራቴጂዎችን ለመፍጥር እድል ይሰጣል በሌሎች የልዩነት ሁኔታዎች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ እድል ይሰጣል።

የዘር እኩልነት ለመፍጠር የሚኖረው ስትራቴጂ በሌሎች ጉዳዩች እኩልነት ለመፍጠር ከሚደረገው ጥረት ይለያል።  አንድ ነገር ለሁሉም ይበቃል የሚል ስትራቴጂ ብዙም ውጤታማ አይሆንም። ትልቅ የሆነ ለውጥ ለማምጣት አትኩሮት እና በአንድ ነገር ላይ ያነጣጠረ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ነው።  ሌሎች የተገለሉ ህብረተሰቦችን የአካዳሚ ውጤታማ ከመሆን የሚይዛቸው ነገር ዘር አንድ ጉዳይ

ሊሆን ይችላል። በተቆላለፈ ሁኔታ የመገለል ሁኔታ ሊኖር የሚችል መሆኑን የሚረዳ አንድ አመለካከት መኖር መረዳት የዘር እኩልነትን በትምህርት ቤት ዲቪዝኑ እና በኮሚዩኒቲው ለማስፈን እገዛ ያደርጋል።

የእኛ ግብ አንድን ሰው ምኞቱን ለማሳካት እና በተሞላ መልኩ በሚፈልጉት መስክ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የትምህርት መስክ ተሳትፎ ለማድረግ እንዲችሉ እንቅፋቶችን በጋራ ማስወገድ ነው።

ፍትሃዊነት እና እኩልነት አንዳንድ ግዜ በተለዋዋጭነት የመጠቀም ሁኔታ ይታያል። ሆኖም ግን የሚያስተላፉት መልእክት ይለያያል። ፍትሃዊነት ስለአግባብነት ተገቢነት ሆኖም እኩልነት ደግሞ ተመሳሳይነት ያሳያል። እኛ ፍላጎት የለንም የውጤት ልዩነትን ማጥበብ የተማሪዎችን ውጤት እኩል በማድረግ። እኛ የምንፈልገው በሁሉም መስክ ለሁሉም ፍትሃዊ የሆነ እድል በመፍጠር እና በትምህርት ቤቶች አሰራር በመፍጠር የእኛ ውጤት ማሳደግ ነው። ፍትሃዊነት ለእኛ ያለው ትርጉም እያንዳንዱ ተማሪ እኛ የት መሆን ይኖርባታል ብለን የምናስበው ሳይሆን ባለበት ስፍራ ደረጃ ማግኘት ማገዝ ነው። አንዳንድ ግዜ ይህ ማለት የማስተማር አቀራረብ መቀየር እንዲሁም እንዴት መልስ እንዴት እንደምንሰጥ እና በማንኛውም የትምህርት አቀባበል ደረጃ ያሉ ተማሪዎችን ድጋፍ ማድረግ ይሆናል። እንዲሁም ለተማሪዎች የማጠናከሪያ እና ከፍ ያለ ደረጃ ትምህርት መስጠት ብዝሃነት ለማስፋት ያለው የትምህርት ደረጃ ዝቅ ሳይል - እንዲያውም ለሁሉም የትምህርት ደረጃውን ከፍ ማድረግን ያካትታል።

ፍትሃዊነት ለሁሉም እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን መነሳሳት ማለት ነው። ከአንድ ቡድን ወስዶ ለሌላ መስጠት ማለት አይደለም። ሁሉም ተማሪዎች በአገልግሎት ተጠቃሚ መሆናቸው፣ በፕሮግራም እና በእድሎች ተጠቃሚ ማድረግ ውጤታማ እንዲሆኑ ማስቻል ነው።

— Government Alliance on Race and Equity (GARE) inspired —

## ቁልፍ ቃላት ትርጎሜ

የዘር ፍትሃዊነት፤ ዘር የአንድ ሰው ህይወት፣ እድል ማግኘት እና ውጤት የማይወስነው መሆን ሲረጋገጥ ነው።

የትምህርት ፍትሃዊነት፤ በዘር፣ በኢኮኖሚ እና በሌላ መስክ ልዮነቶች ምክንያት የሚኖረው የትምህርት ልዮነት እንዲቀንስ እና እንዲወገድ ማድረግ ነው። ጥሩ የትምህርት ውጤቶች በፍትሃዊነት በተመጣጣነ መልኩ በሁሉም የህብረተሰብ አካል እና በተለያዮ ቡድኖች መዳረስ ይኖርበታል። ጥሩ ያልሆኑ አሉታዊ ውጤቶች እና ተመጣጣኝ ያልሆኑ ሁኔታዎች ለሁሉም ቡድኖች አካሎች እንዲቀንሱ ማድረግ።

የትምህርት ጥራት፤ በምናከናውናቸው ስራዎች ሁሉ ደረጃቸውን ከፍ እናደርጋለን። ተማሪዎች ለህይወት የተዘጋጁ እና የሚያገናዝቡ ዜጎች እንዲሆኑ እናስተምራለን። ተማሪዎችን እና ሰራተኞች ማንነታቸው እና ባህላቸውን እንዲጠብቁ ድጋፍ እናደርጋለን። ትእዛዝ ተከታይ እና የፈተና ውጤት ከማግኘት ይልቅ ይዘት፣ ጥልቀት እና የጠለቀ ሃሳብን መፍጠር በጣም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው ።

# የእኛ ዋና አምነቶች

## አስተናጋጅ ተቀባይነት

ሁሉም ባለጉዳዮች በትምህርት ቤቶች መገኘታቸው መልካም አቀባበል እንደሚያገኙ እንዲሰማቸው በትጋት እንሰራለን። በእኛ በር የገባውን ሁሉ እናስተናግዳለን እና ያለንን ልዩነት እንቀበላለን ምክንያቱም ያለን ልዩነት ትልቁ ጥንካሬያችን እንደሆነ እንረዳለን።

## ፍትሃዊነት ላይ ማተኮር

ትምህርት ለማግኘት ያሉ እንቅፋቶችን ለማስወገድ በትጋት እንሰራለን።

### ምቹ ሁኔታ ኋይል መፍጠር

እኛ እያንዳንዱን ተማሪ እና ሰራተኛ የተሻለ ውጤት እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ እንፈጥራለን።

### አዲስ  ፈጣሪዎች

እኛ በክፍል ውስጥ እና በአጠቃላይ በትምህርት ስርዓቱ የሚታዮ ችግሮችን መፍትሄ ለማግኘት እንቀሳቀሳለን።

### ውጤት ላይ ማተኮር

እኛ ለመማር፣ለማደግ፣ እና ከፍ ባለ ደረጃ ውጤት ለማግኘት ትልቅ ግቦችን እቅድ እናዘጋጃለን።

# የተግባር መርሕ

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ስትራቴጂውን፣ ስርዓቱን አቅሙን ሪሶዋርሱን ከተግባር መርሀ ጋር እንዲጣጣም ያደርጋል። ይህም እንዴት ትምህርት ቤቶችን እንደምንመራ፣ የተማሪዎችን ውጤት  እንዴት እንደምናሳድግ እና በዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ ያሉ ተማሪዎች፣ ጥቁር እና የስፓኒሽ ማህበረሰብ አባላት ተማሪዎች፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋ (EL) ተማሪዎች እና የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች የውጤት ልዩነቶችን ማስወገድ አቅጣጫ የሚያሲዙ መርሆች ይኖሩታል።  ይህም ለእኛ ውጤት ለማግኘት፣ የእኛ ተልእኮ መፈፀማችንና ዋና እምነቶች ለመከተል ያስችለናል።

በኤ.ሲ.ፔ.ኤስ. የእኛ የተግባር መርሕ የተመሰረቱ በሚከተሉት ሃሳቦች ላይ ነው፤

1. ርእሰመምህራን የትምህርቱ መሪዎች ናቸው። እንደ አሰራር  የእኛ አስተማሪዎች እና ሰራተኞች ማገዝ ይኖርብናል የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎት የሚያሞላ የተጠናከረ ስርዓተትምህርት በማዘጋጀት -- በተለይም በዝቅተኛ ደረጃ ተጠቃሚ የነበሩትን -- እና ለእኛ ርእሰመምህራን በየትምህርት ቤቶቻቸው የትምህርት መሪዎች ለመሆን የሚያስችላቸውን ተገቢውን መገልገያ መሳሪያ እና ሪሶዋርስ መስጠት።

2. የማእከላዊ  ጽ/ቤት ድርሻ  በሁሉም ትምህርት ቤቶች መከናወን ያለባቸውን የተመረጡ ነገሮች አትኩሮት በመስጠት የተማሪዎች ውጤት ማሳደግ እና የእድል እና የውጤት ልዩነት ማስወገድ ለትምህርት ቤቶቻችን ድጋፍ ማድረግ ይሆናል። የማእከላዊ  ጽ/ቤት ድርሻ ያለውን ውስን አቅም በስትራቴጂ በመጠቀም ሁሉም ትምህርት ቤቶች በትክክል ምንም የማይለያይ በመላው የትምህርት ቤት አስተዳደር ዲቪዝን አትኩሮት የሚሰጣቸውን በአግባቡ መፈፀም ይሆናል።

3. ምንም እንኳን የመላው ትምህርት አስተዳደር ክልል አትኩሮት ሊቀያየር የሚችል ቢሆንም በርካታ ዋና መርሆዎች የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱን እና አፈፃፀም የሚመሩ ይሆናሉ።
    a. በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የትምህርት ቤት ቦርድ የተዘጋጁት ዋነኛ እምነቶች እና በስትራቴጂክ እቅዶች የተካተቱት የሁሉንም ሰራተኞች፣ አስተማሪዎችን፣ የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ እና የትምህርት ቤት ቦርድ ተግባራትን አቅጣጫ የሚያሲዙ ናቸው።
    b. በአስተዳደር ዲቪዥኑ የትኩረት መስክ የሚጠናቀቀው በትምህርት ቤት ጉዳዩ ከሚለመለከታቸው ወገኖች ጋር በመካከር ይሆናል።
    c. የአስተዳደር ዲቪዥኑ የትኩረት መስክ በሚገባ የታወቀ እና በፅሁፍ የተዘጋጀ የተገለፀ ይሆናል እና በአግባቡ ተግባራዊ ሊሆን  እና ለመከታተል የሚያስችል ሪሶዋርድ ድጋፍ የያዘ ይሆናል።
    d. የሙያ ትምህርት፣ ትምህርት አሰጣጥ እና የአመማራር ስልጠና እና በሱፐርኢንቴንደንት ከት/ቤት የትምህርት እና የዲፓርትሜንት ኋላፊዎች ጋር የሚደረግ የሶስት ወር እቅድ የማሻሻያ ስብሰባ በመላ የትምህርት ዲቪዝኑ  ያተኮረ ይሆናል።

e. የትምህርት ቤት ዲቪዝኑ አትኩሮት ከሰጠው ጉዳይ ውጭ አዲስ የትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ሲኖር የማእከላዊ ጽ/ቤት የሚያቀርበው ሃሳብ ከትምህርት ቤት ጉዳዩ በሚመለከታቸው በኩል ይታያል እና - አስፋላጊ ከሆነ- በተወሰኑ ቁጥር ባላቸው ት/ቤቶች በሙከራ ሊካሄድ ይችላል። በጥንቃቄ ግምገማ ከተደረገ በኋላ ነው የትኩራት አቅጣጫ በስፋት ለማካሄድ ጥረት የሚደረገው።

f. የትምህርት ቤት ዲቪዝኑ አትኩሮት ከሰጠው ጉዳይ ውጭ  የተማሪዎችን ፍላጎት ለማሞላት እና የእድል እና የውጤት ልዩነት ለማጥፋት ት/ቤቶች ከቤተሰቦች ጋር እንዲሰሩ ይበረታታሉ። የማእከላዊ ጽ/ቤት ለት/ቤቶች ድጋፍ ያደርጋል የሚሰሩ የፈጠራ ስራዎችን ለመለየት እና -- ተገቢው የማጣራት ስራ ከተካሄደ በኋላ፣ ትንተና እና ተፅእኖ የሚፈጥሩ ሂደቶችን -- ካካተተ ተገቢ ውጤታማ የሆኑ አሰራሮችን በትኩረት አቅጣጫ ውስጥ እንዲካተቱ ይደረጋል።

4. በመላ ዲቪዝን ለ2020-25 የትምህርት ዘመን የትኩረት አቅጣጫ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፤
   - ተመዛዛኝ የሆነ መሰረታዊ እውቀት (ባላንስድ ሊተርሲ)
   - ማህበራዊ፣ ስሜት እና የአካዳሚ ትምህርት(SEAL)
   - የቤተሰብ ተሳትፎ
   - ባለብዙ ደረጃ የድጋፎች ሥርዓት(MTSS) እና የቅድሚያ የማስጠንቀቂያ ስርዓት ማዘጋጀት ለተማሪዎች የትምህርት  እና የባህሪ ፍላጎት ድጋፍ ለማድረግ እና በተደጋጋሚ የመቅረት ችግር ምክንያቶች ጭምር።
   - በርካታ መንገዶች ማዘጋጀት ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ለማግኘት እና ከዚያም ባሻገር

5. የትምህርት ቤት ዲቪዝኑ አትኩሮት ከሰጠው ጉዳይ ውጭ ርእሰ መምህራና የእነርሱ የአመራር ቡድን ድጋፍ ያገኛሉ ሌሎች ስትራቴጂዋችን በማዘጋጀት፣ በስራ በማዋል እና በመቆጣጠር -- በራሳቸው የትምህርት ቤት ማሻሻያ እቅዶች በግልፅ የተዘጋጁ -- በተለይም በተለምዶ ሁኔታ አግባቡ ተጠቃሚ ያልሆኑትን ተማሪዎችን ፍላጎት የሚያማሉ።

እኛ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ይህን ሁኔታ እና ዝርዝር ሁኔታ በዚህ የተግባር መርሕ እናጠቃልለዋለን።

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ጥራት ያለው ትምህርት እና የተለያየ ድጋፍ ፣ ኮሚዩኒቲውና ቤተሰቦችን ማሳተፍ እና ተገቢው ሪሶዋርስ ድጋፍ፣ እድሎችና በፍትሃዊ መልኩ  በመመደብ የውጤት ልዩነቶችን በተለይ ቀደም ሲል ተጠቃሚ ባልሆኑ የተማሪ አካላት እዲጠፉ ማገዝ እና ተማሪዎች ከከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሲጨርሱ ለኮሌጅ፣ ለስራ እና የህይወት ዝግጁ እንዲሆኑ በማስቻል እገዛ ያደርጋል። ጥራት ያለው ትምህርት መስጠቱን ለማረጋገጥ እና የተለያዩ ድጋፎችን ለማድረግ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የሚከተሉትን ያከናውናል፤

- በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችና ቤተሰቦችን ማሳተፍ፣
- በሁሉም ት/ቤቶች በስራ እንዲውሉ የተመረጡ ስራቴጂዎች  መለየት፣ ድጋፍ ማድረግ እና መቆጣጣር።
- ርእሰ መምህሮች እና የእነርሱ አመራሮችን ቡድን ተጨማሪ የተማሪዎች ልዩ ፍላጎቶችን ለማሞላት የሚያስችላቸውን ስትራቴጂዋችን በስራ ማዋል እንዲችሉ አቅሙን መፍጠር።

ይህን የተግባር መርሕ በስራ ለማዋል ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ግቦችን፣ መለኪያ መስፈርቶችን፣ ስትራቴጂዋችን እና የተመረጡ ተግባራት አዘጋጅቶል፤  ውጤት በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ዲፓርትሜንቶች መካከል በቅንጅት መስራትን ይጠይቃል ት/ቤቶችና ቤተሰቦችን ለመደገፍ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሞክሩ ለማድረግ በተለያየ እና ተለዋዋጭነት ባለው አለም አቅም ማግኘታቸው ለማረጋገጥ።

# የእኛን ውጤት መመዘን

እያንዳንዳቸው የስትራቴጂክ እቅድ አምስት ግቦች መሳካታቸውን ለመመዝንና ሪፓርት ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ መስፈርቶች አሎቸው።

ዋነኛ የክንውን አመልካች(KPIs) ድርጅቱ ለማግኘት የሚሞክረውን ግብ የሚያመለክት ዋና አጠቃላይ ውጤት የሚያሳዩ ናቸው። ውጤታማ መሆን ምን ማለት እንደሆነ የሚያሳዮ እና በትክክል ለውጥ እያሳየን እንደሆነ ለመረዳት እንዴት እንደምናውቅ መልስ የሚሰጡ ናቸው። እንደ አንድ የትምህርት ድርጅት በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሁሉም ዋነኛ የክንውን አመልካች(KPIs) የተማሪዎች ውጤት ናቸው።

ከመለኪያዋቹ በተጨማሪ እያንዳንዱ ግብ እና ተግባራዊ የሚሆኑ ጉዳዮች ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. እነዚህ ግቦች ለማሳካት የሚወስዳቸውን እርምጃዋች የሚያሳዮ የየራሳቸው የተለያዮ ስትራቴጂዋች አሎቸው።

እኛ የእድል እና የውጤት ልዩነቶች መወገዳቸውን ለማረጋገጥ የምናሳየውን እድገት በሚከተሉት መንገዶች ክትትል እናደርጋለን፤

- የመዋእለ ህፃናት ዝግጁነት
- የተማሪዋች እድገት እና የንባብ ብቃት
- የተማሪዋች እድገት እና የሂሳብ ትምህርት ብቃት
- በተከታታይ ትምህርት የሚያቆርጡ ተማሪዋች ተመጣጣኝ አለመሆን
- የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች መጠን ተመጣጣን አለመሆን
- በአራት ዓመት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚያጠናቅቁ የ9ኛ ክፍል ተማሪዋች የመቶኛ ድርሻ በትክክል በታሰበው መሰረት መሆን
- በተለምዶ በቂ ውክልና ከሌላቸው በአድቫንስ ኮርሶች የሚከታተሉ ተማሪዋች ብዛት ተሳትፎ ሚዛናዊ አለመሆን።

# የእኛ 5 ግቦች፤

ስልታዊ ማስተካከል (ሲስተሚክ አላይንሜንት)

የትምህርት አሰጣጥ ጥራት

የተማሪዋች እድል ማግኘት እና ድጋፍ

የስትራቴጂክ ሪሶዋርስ ድጋፍ አመዳደብ

የቤተሰብና የማህበረሰብ ተሳትፎ፤

# ስልታዊ ማስተካከል (ሲስተሚክ አላይንሜንት)

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ቀጣይ የሆነ የማሻሻል ባህል እና ለትምህርት ቤቶችና የትምህርት አሰጣጥን ማሻሻያ ፍትሃዊ የሆነ ስርዓት አሰራር ይገነባል።

የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. **ሲስተም** ስርዓት የሚከተሉትን ገፅታ ይኖረዋል፤

- ከኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ተልእኮ ጋር የተቀናጀ ይሆናል።
- ግልጽ የሆነ፣ ምጥን ያለ፣ ለተማሪዋች ውጤት የሚያስገኙ ስርዓትአቀፍ የተለዪ የማስተማሪያ ማሻሻያዋችን ለመለየት የሚያስችል ግንዛቤ የሚፈጥር እይታው በግልፅ እንዲታወቅ ያደርጋል።
- አትኩሮት እንዲኖር፣ አቅም እና ሪሶዋርስ በተወሰኑ አትኩሮት በሚሰጣቸው ስትራቴጂክ ጉዳዮች ላይ እንዲውል ሁሉም ት/ቤቶች በአትክሮት የሚፈፅሞቸው እንዲሆን ማድረግ።
- የአስተዳደር ዲቪዝኑ መሪዋች ለትምህርት ቤቶችና ለትምህርት ቤት መሪዋች የትብብር ድጋፍ እንዲያደርጉ ፣ ቅንጅት እና የቁጥጥር ስራ እንዲደረግ ውጤታማ መሆን እንዲያስችል ለማረጋገጥ ያስችላል።

## መለኪያዎች

እኛ የእድል እና የውጤት ልዩነቶች መወገዳቸውን ለማረጋገጥ የምናሳየውን እድገት ለመረዳት በሚከተሉት መንገዶች ክትትል እናደርጋለን፤

- የትምህርት ቤት አስተዳደር ዲቪዝን ተመረጡ ስትራቴጂክ የአትኩሮት አካባቢያዎችን በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሰራተኞች፣ በተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና ሰፊው ህብረተሰብ (መጠይቅ) መደገፍ።
- ለት/ቤት አስተዳደር ዲቪዝን ስልታዊ ማስተካከል (ሲስተሚክ አላይንሜንት) እና የተለዩ ስትራቴጂክ ትኩረት የሚሰጣቸው ከኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሰራተኞች አስተያየት ግብዓት እና ድጋፍ ማግኘት (መጠይቅ)
- የትምህርት  ቤት ሰራተኛ ሪፖርት ቅንጅት፣ ቁጥጥር እና ድጋፍ ከማእከላዊ ጽ/ቤት (መጠይቅ)
- የአፈፃፀም ደረጃ የስትራቴጂክ ትኩረት የሚሰጣቸው በእያንዳንዱ ት/ቤት እና ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ዋና ጽ/ቤት ዲፓርትሜንቶች።

## ስትራቴጂ  እና  የተመረጡ  ተግባራት

ትምህርት ቤቶች በራሳቸው መንገድ የሚፈፅማቸውን ጉዳዩች እና ያልሆኑትን  ሁኔታዎች በግልፅ ማስቀመጥ እና በአንፃሩ የሚኖሩትን ድርሻዎችን እና ኋላፊነቶች ለአስተዳደር እና ለትምህርት ባለሞያዎች ማስቀመጥ።

- ከኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ዋና ጽ/ቤት ድጋፍ በማግኘት ሁሉም ትምህርት ቤቶችን የሚፈፅሞቸውን አትኩሮት የሚሰጣቸውን ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች በግልፅ ማስቀመጥ።
- አፈፃፀማቸውን እና ቁጥጥር ለመደገፍ የሚያስችል ግልፅ አሰራሮችን ማዘጋጀት።
- ከማእከላዊ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ትኩረት የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ውጤታማ የሆነ አሰራር እና በቁጥጥር እንዲኖር ማድረግ።
- የትምህርት አስተዳደር ዲቪዝን የሙያ ትምህርት ፤ የስትራቴጂክ ጉዳዩችን አፈፃፀም ላይ እንዲያተኩር ማድረግ።
- በገልፅ የተቀመጠ የትምህርት አመራር ኋላፊነት እና አሰራር ሂደት ለትምህርት ቤቶች እና ለኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ዋና ጽ/ቤት አመራሮች።

የትምህርት አስተዳደር ዲቭዝኑን ወደ ትምህርት ተቋም መቀየር።

- አዲስ የትኩረት አካባቢዎችን በሙከራ ማየት በአስተዳደር ዲቪዝኑ በመላው ተግባራዊ ከማድረግ በፊት።
- በአስተዳደር ዲቪዝኑ እና በትምህርት ቤቶች አሰራር እና አደረጃጀት ማዘጋጀት ከፍተኛ አቅም ላላቸው ተማሪዎች ዋና እንቅፋቶች የሚሆኑ ነገሮች መለየት እና “ማቀድ- ማድረግ -ማጥናት-ማከናወን” የማሻሻል ዑደቶችን ማስፈፀም።
- በተዘጋጁ መስፈርቶች መሰረት ከሌሎች በበለጠ የሚያከናውኑ ትምህርት ቤቶችን እና ፕሮግራሞች መለየት እንዲሁም ስራቸውን በሌሎች ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች እንዲካሄድ ማመቻቸት የአሰራር ፕሮቶኮል በማዘጋጀት ፣ በማሰልጠን እና ቅንጅት በመፍጠር ።
- ለዋና የዲቪዝን የትኩረት አቅጣጫዎች መለኪያ መስፈርቶችን ማዘጋጀት በስራ ማዋል።

ስለታየው ለውጥ እና የስትራቴጂክ እቅድ አፈጻፀም  ስለተገኘው ውጤት መደበኛ የሆነ ወቅታዊ መረጃ ማሰጠት።

- ስለተማሪዎች የአካዳሚ ለውጥ እና አትኩሮት የሚሰጣቸው ስትራቴጂክ ትኩረት ጉዳዩች አፈጻፀም በተለይ በተማሪዎች ለውጥ ላይ ያተኮረ ለቦርድ መደበኛ የሆነ፣ ወቅታዊ መረጃ ማቅረብ።

የዲቪዝኑ የስራ አስፈጻሚ ዲፓርትሜንቶች ስራዎች በቅንጅት የሚሰሩበትን ባህል መፍጠር እና ቤተሰቦችን ለተማሪዎችን ድጋፍ እንዲያደርጉ እንዲሳተፉ ማድረግ።

- በትምህርት ቤት ግቢዎች እና በስራ ማስኬጃዎች የተመረጡ ተግባራትን እና ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት በደህንነት እና ጥበቃ ፣ንፅህና፣ የዲቪዝን ተቆማትና እና ጤናማነት ማዘጋጀት።

- ስለትራንስፖርት፣ የተመጣጠነ ምግብ፣ የተቆማት አገልግሎት፣ ደህንነት እና ጥበቃ ግልፅ መልእክት፣ የተተረጎመ፣ አሳታፊ እና መረዳት የሚቻል እና ወቅታዊ እንዲሆን ማድረግ።
- የትምህርት ቤት/ተማሪ ስልጠና እና ጠቃሚ የስራ አፈፃፀም ረገድ ቆሚነት ያለው ስልጠና ማዘጋጀት።

# የትምህርት አሰጣጥ ብቃት

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያለው የትምህርት አሰጣጥ በበቂ ሁኔታ ማግኘት እና የማሳተፍ የሚችሉበትን ያረጋግጣል።

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የትምህርት አሰጣጥ ፤

- ከመላ ዲቪዝን የትምህርት አሰጣጥ አቅጣጫ እና ከፍተኛ ጥራት ያለው ስርዓተ ትምህርት ጋር እንዲጣጣም ማድረግ።
- አሳታፊ እና ጠንካራ እንዲሆን ማድረግ።
- ከባህሉ ጋር የተገናዘበ ማድረግ።
- ከተማሪዎች አቅም ጋር የተገናዘበ ማድረግ።
- ከተማሪዎች ማህበራዊ፣ ስሜት እና የአካዳሚ ፍላጎቶች ጋር የሚሄድ ማድረግ።
- በት/ቤት ዲቪዝኑ አመራሮች እና የትምህርት አስልጣኞች የሚደገፍ እና ቁጥጥር የሚደረግበት አንድ ይዘት ያለው ባህል ፣ጥልቀት ያለው፣ ጥልቅ የሆነ አስተሳሰብ እና የትምህርት አሰጣጥ መፍጠር።

## መለኪያዎች

እኛ የእድል እና የውጤት ልዩነቶች መወገዳቸውን ለማረጋገጥ የምናሳየውን እድገት በሚከተሉት መንገዶች ክትትል እናደርጋለን፤

- የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የትምህርት አሰጣጥ ማእቀፎችን (ምልከታዎች) በመጠቀም የትምህርት እቅድ የሚያዘጋጁ ከአስተማሪዎች መካከል በመቶኛ ምን ያህል እንደሆኑ መረዳት።
- በእያንዳንዱ ት/ቤት ከፍተኛ ውጤት የሚያስመዘግቡ ክፍሎችን ምን ያህል እንደሆኑ በመቶኛ ፐርሰንት ማወቅ (አሳታፊ፣ ጠንካራ፣ ከባህል አንፃር ተገቢ የሆኑ) ስትራቴጂዎች በመጠቀም (ምልከታ እና ዝርዝር መስፈርቶች(ሩብሪክ) ።
- በትምህርት ቤት ወይም በትምህርት አስተዳደር ደረጃ በሚሰጥ በመመዘኛ ፈተና መሰረት የተማሪዎችን ለውጥ መረዳት።
- አስተማሪዎች ጥራት ባለው ስልጠና እና ድጋፍ ማግኘታቸውን የሚገልፁ የአስተማሪዎች መጠን በመቶኛ ማወቅ (መጠይቅ)
- ተማሪዎች በማህበራዊ፣ስሜት እና የአካድሚ ድጋፍ ማግኘታቸውን ሃሳባቸውን የሚገልፁ የተማሪዎችን ብዛት በመቶኛ ፐርሰንት ማወቅ (የፍትሃዊነት ኦዲት)
- ልጆቻቸው ጥራት ያለው ትምህርት እያገኙ መሆናቸውን የሚገልፁ ወላጆች ምን ያህል እንደሆኑ በመቶኛ ፐርሰንት ማወቅ (መጠይቅ)

## ስትራቴጂ  እና  የተመረጡ ተግባራት

አስተማማኝ የሆነ እና ተገቢነት ያለው ስርዓተ ትምህርት ለሁሉም ተማሪዎች ማቅረብ ማረጋገጥ።

- የትምህርት ቤት አስተዳደር ዲቪዝን ስርዓተ ትምህርት ግምገማ በስራ ማዋል።
- የትምህርት አሰጣጥ አሰራር ማእቀፉን ለማሻሻል እና አጠቃቀሙን ለማረጋገጥ ከትምህርት ባለሞያዎች ጋር በቅንጅት መስራት።
- የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎችና የእንግሊዘኛ ቋንቋ (EL) ተማሪዎች ለማስተማር የተሻለ የተመረጡ አሰራሮችን በስራ ማዋል።

- ልዩ ስጦታ እና ችሎታ ያላቸው እና የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች እቅድ በስራ ማዋል ስርዓተ ትምህርቱ የግል የተማሪዎች ፍላጎት የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ።

ጥቂት በግልፅ የተቀመጡ ከፍተኛ ውጤት ያላቸው የማስተማር ስትራቴጂዎች በስራ ማዋል የአካዳሚ፣ ትምህርት እና የማህበራዊ እና የስሜት ድጋፎችን ለተለያዪ የተማሪው ህብረተሰብ ማቅረብ።

- ከፍተኛ ውጤት የሚያስገኙ የትምርህት አሰጣጥ ስትራቴጂዎችን እና የሚጠበቁ ነገሮችን በዲቪዝን ደረጃ መጠቀም።
- ሁሉም ትምህርት ቤቶች የስትራቴጂዎችን አፀፈፃፀም ድጋፍ እና ክትትል እንዲያደርጉ።
- የሙያ ትምህርት ስልጠና ፣ ለትምህርት ቤቶች የሚሰጡ የዲቪዝን ድጋፎችን እና የትምህርት ስልጠና በትምህርት አሰጣጥ ማእቀፍ ላይ በመመስረት እና ከፍተኛ ውጤታማነት ያላቸውን የትምህርት አሰጣጥ ስትራቴጂዎች በተገቢ ሁኔታ አንፃር በመመለከት መለየት።
- የትምህርት አሰጣጥ እና ሂደቶችን በስራ ማዋል እና ማሳደግ እና አፀፃፀምና ያስገኘውን ውጤት መገምገም።

በመላው የትምህርት ዲቪዝን የK-2 ድረስ ክፍሎች ወጥነት ያለው፣ ከፍተኛ ውጤት የሚያስገኝ አቀራረብ መሰረታዊ የንባብ ትምህርት በስራ ማዋል።

- በግልፅ በመለየት እና በማስረጃ ላይ የተመሰረተ የንባብ አቀራረብ የK-5 የንባብ መመሪያዎች በመከተል የስራ አፈፃፀሙን መደገፍ።
- የK-2 የንባብ ግብረሃይል ቅፅ ከሁሉም የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ት/ቤቶች ውክልና ያካተተ ለቅንጅት፣ለምርምር እና ምርጥ የሆነ የንባብ ስራ አፈፃፀም ሂደቶችን በስራ ማዋል።
- አዲስ የK-5 የንባብ አሰራር በስራ ማዋል፣ የTCRWP Fountas እና በፓናል የሚመራ የአነባበብ ዘዴዎችና የቃላት ጥናት የሙያ ትምህርት ስልጠና መስጠት።

ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮጀክት በስራ ማዋል

- ለተማሪዎች እድል ለመፍጠር የተለያየ የሙያ መስክ ጋር እንዲተዋወቁ የሚያግዙ የኢንዱስትሪ አማካሪ ቦርድ አጋሮችን መደገፍ።
- ለሚኒ ሐዋርድ እና ለኪንግ ስትሪት ግቢ የትምህርት ቀረፃ ቡድን ፕሮግራም ዝግጅት በመምረጥ የሚያግዙ መለየት።
- በሚኒ ሐዋርድ ግቢ የሚሰጡ የትምህርት መስፈርቶችን ማጠናቀቅ።
- በሚኒ ሐዋርድ ግቢ አዲስ ግንባታ ማስጀመር።
- ዋና የግዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት ለአመራሩ እንደሁኔታው ተለዋዋጭ ነገሮችን በቲ.ሲ. ዊሊያምስ ማዘጋጀት።
- የአማርኛ እና የአረብኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎት ምን ያህል እንደሆነ ጥናት ማካሄድ።

የብዝሃነት ጥንካሬ እና የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ተማሪዎች ፍላጎት የሚያማላ ባለብዙ ደረጃ የድጋፎች ሥርዓት(MTSS) አፈፃፀም በስራ ማዋል።

- ወጥ የሆነ፣ ከፍተኛ ውጤት ያለው የትምህርት አሰጣጥ አሰራር ለሁሉም ተማሪዎች በ1፣2 እና 3ኛ ደረጃ ተገቢው ክትትል የሚደረግበት የአፈፃፀሙን ተገቢነት ለመከታተል የሚያስችል የሚጠበቁ ውጤቶችን የሚያሳይ ማዘጋጀት።
- በየት/ቤቱ ያሉ ከMTSS ቡድን ከመረጃ-ወደ-ተግባር ላይ የተመሰረተ አፈፃፀም፣ ብቃት ያለው እና ውጤታማ የሆነ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት መረጃ መስጠት ቀጣይነት ያለው ትምህርት እና ለውጥ ለማስገኘት
- ጠቀሚ አመላካች፣ ፎርማቲቭ እና ሰሚትቭ የሆኑ የፈተና መረጃዎች ውጤቶችን በመጠቀም ተገቢውን የድጋፍ ጣልቃ መግባት ወይም ስትራቴጂዎችን ማዘጋጀት።

የተሻለ ምርጥ አሰራሮችን መለየት በኦንላይን ሆነ በድብልቅ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴዎች በመለየት፣ በመደገፍ እና ለትምህርት አገልግሎት የሚሰጥበት እና ፈጠራን ማሳደግ።

- የሳታላይት ፕሮግራም እንዲስፋፋ ማድረግ።
- በኦንላይን እና የድብልቅ ትምህርት አሰጣጥ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮጀክት እንዲቀናጅ ማድረግ።
- የተሻለ ኮሚዩኒኬሽን ግንኙነት ከቤተሰቦች እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ጋር እንዲኖር ለማድረግ ለመፍጠር የቴክኒዎሎጂ መሳሪያዎች አጠቃቀም ማሻሻል።

# የተማሪዎች እድል ማግኘት እና ድጋፍ

ተማሪዎች ፍትሃዊ የሆነ እና አሳታፊ የሆነ ፕሮግራሞችና ድጋፎች ማግኘታቸውንና የመማር እድል ለማግኘት እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን የሚቀንስ መሆኑን ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ያረጋግጣል።"

የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ፕሮግራም እና ድጋፍ፤

- የተሞላ የልጅ እድገት ጥንካሬና እስፈላጊነትን ይረዳል።
- ሁሉም ተማሪዎች የተሻለ ከፍተኛ ውጤት እንዲያሳዩ መጠበቅ እና መደገፍ።
- ተማሪዎች አሳታፊ ማድረግ እና የትምህርቱ ባለቤትነት እንዲሰማቸው ማበረታታት።
- ተማሪዎች ከሁለተኛ ደርጃ ባሻገር እንዲመለከቱ መንገዱን ማሳየት።

## መለኪያዎች

እኛ የእድል እና የውጤት ልዩነቶች መወገዳቸውን ለማረጋገጥ የምናሳየውን እድገት በሚከተሉት መንገዶች ክትትል እናደርጋለን፤

- የፍትሃዊነት ኦዲት (መጠይቅ)
- በአንደኛ ደረጃ ያሉ የTAG ተማሪዎች በትምህርት ቤት ደረጃ እና በተማሪዎች ቡድን ደረጃ ያለውን ያልተመጣጠነ ሁኔታ የሚያሳይ የመቶኛ ፐርሰንት ስሌት።
- በሁለተኛ ደረጃ ያሉ በከፍተኛ ደረጃ የሚሰጡ ኮርሶች የሚከታተሉ በትምህርት ቤት ደረጃ እና በተማሪዎች ቡድን ደረጃ ያለውን ያልተመጣጠነ ሁኔታ የሚያሳይ የመቶኛ ፐርሰንት ስሌት።
- በት/ቤት  እና በተማሪዎች ቡድን ደረጃ ከት/ቤት በብዛት በተደጋጋሚ የሚቀሩ ተማሪዎች ብዛት የሚያሳይ የመቶኛ ፐርሰንት ስሌት።
- በት/ቤት እና በተማሪዎች ዘር/ብሔረሰብ ደረጃ ወደ ልዩ ትምህርት አገልግሎት የሚላኩ ተማሪዎች ብዛት የሚያሳይ የመቶኛ ፐርሰንት ስሌት።
- ደህንነት የሚሰማቸው፣ ዋጋ እንደሚሰጣቸው የሚያውቁ እና በትምህርት ሂደት ተሳታፊ የሆኑ ተማሪዎች መጠን የመቶኛ ፐርሰንት ስሌት።(መጠይቅ)
- በተማሪዎች ደረጃ የሚያቆርጡ ብዛት መጠን።
- የእገዳ መጠን (ከትምህርት ቤት ውጭ እና በትምህርት ቤት ውስጥ) በትምህርት ቤት እና በተማሪዎች ቡድን የማይመጣጠን ደረጃ የመቶኛ ፐርሰንት ስሌት።
- በድብልቅ የትምህርት አሰጣጥ (በስቴት እና በፌደራል የገንዘብ) ወይም በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ቅድመ-መዋእለ ህፃናት ፕሮግራም የሚሳተፉ የተማሪዎች ቁጥር።

## ስትራቴጂ እና የተመረጡ ተግባራት

ተማሪዎችን እና ቤተሰቦች ተሳታፊ ማድረግ፣ አስፈላጊ ድጋፎችን እና አገልግሎቶችን በመምረጥ እና በትምህርት ቤት መስጠት ያሉትንና አዲስ ሪሶዋርሶችን ኢጋዥ አጠቃቀም መከታተል።

- በሁሉም ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ድጋፍ መስጠት በሚታየው የፍላጎት ግምገማ መሰረት በትምህርት ቤት የግዜ ሰሌዳ አወጣጥ መሰረት የማሻሻያ እርምት (ሪስቶራቲቭ) አሰራሮች በመከተል የማህበራዊ፣ ስሜት እና የአካዳሚ ትምህርት(SEAL) ማዘጋጀት እና የኮሚዩኒቲ አጋዝ ቡድኖች በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በየትምህርት ቤቱ ማዘጋጀት።
- ከአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት፣ ከአሌክሳንደሪያ ኮሚዩኒቲ እና የሰብአዊ አገልግሎቶች ዲፓርትሜንት እና የከተማው እና የኮሚዮኒቲ ድርጅቶች ጋር መስራት የተማሪዎች የአእምሮ ጤና እና የህክምና አገልግሎት ድጋፍ የሚያገኙበትን ማመቻቸት።
- በጋራ የእቅድ ዝግጅት ሂደት አማካኝነት የአገልግሎት አሰጥጥ ማስተካከል እና መቆጣጠር ።
- በየትምህርት ቤቱ በተለይ ለአደጋ ሊጋለጡ የሚችሉ የተመረጡ ተማሪዎችን ቡድን ጉዳይ ለይቶ የመከታተል አሰራር ሂደት መከተል።

የማሻሻያ ሳይንስ በመጠቀም መለየት እና ታሪካዊ ስርዓታዊ ኢፍትሃዊነት የፈጠሩ ዋነኛ ምክንያት የሆኑ ነገሮችን መፍትሄ የማፈላለግ ስራ ማከናወን።

- የልዩ ትምህርት አገልግሎት ተመጣጣኝ ያልሆኑ ድርሻዎችን ማጥናት፣ የቅጣት አሰጣጥ፣ የቅደመዋእለ ህፃናት ትምህርት፣ በትምህርት አለመገኘትን የከፋ ተደጋጋሚ ሁኔታ፣ ልዩ ስጦታ እኛ ችሎታ(TAG) ፕሮግራም ዝግጅት፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ደረጃ አድቫንስ ኮርሶች አሰጣጥ፣ የአድቫንስ ዲፕሎማ ማግኘት እና ከሁለተኛ ደረጃ ባሻገር ተሳትፎ እና ዝቅተኛ ድጋፍ የሚያገኙ የተማሪዎች ቡድን ትምህርት የመጨረስ ደረጃ ማጥናት።

በዚህ ቁልፍ በሆነ የትምህርት ጉዞዋቸው የሽግግር ወቅት የተማሪዎች እና የቤተሰቦችን ልምድ ማሻሻል።

- የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎችን እና የክፍል ደረጃ ንግግር ማዘጋጀት ከተማሪዎችና ከቤተሰቦች ጋር ቁልፍ የቅድመ መዋእለ ህጻናት - 12ኛ ክፍል ሽግግር፣ የተማሪዎች የትምህርት አፈፃፀም መረጃ ጭምር ልውውጥ ማካሄድ የአጭር እና የረዥም ግዜ የአካዳሚ እና የማህበራዊ ጉዳይ ግብ የተሻለ ውጤት ለማግኘት መፍጠር።
- ከCTE እና AVID በማቀናጀት የመረጃ ማሰራጫ መገልገያዎችን እና የፕሮግራም ዝግጅቶችን ማዘጋጀት፣ ተማሪዎችና ቤተሰቦች ከሁለተኛ ደረጃ ባሻገር እንዲቀጥሉ ኮሌጅ፣ ከፍተኛ ደረጃ ስልጠና ፣ የውትድርና አገልግሎት፣ የእረፍት መውሰጃ ግዜ እና የስራ ሙያ ምርጫዎች ሽግግር መደገፍ።
- ቀጣይነት ያለው አሰራር ማሳደግ እና በስራ ማዋል ለሁሉም ተማሪዎች በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ግቢዎች ከመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት በመጀመር በአካል በመገኘት ያሉ ፕሮግራሞችን፣ ድጋፍ ሪሶዋርስ እና ድጋፎችን ማስተዋወቅ።
- ከአካዳሚ እና የሙያ ዘርፍ ዝርዝር ፓርትፎሊዬ ፣ የቨርጂኒያ ትምህርት ዲፓርትሜንት የአካዳሚና የሙያ እቅድ መመሪያዎችን ጋር የሚጣጣም የK-12 ኮሌጅ እና የሙያ ፕሮግራም ማዘጋጀትና በስራ እንዲውል ማድረግ ።
- የአካዳሚ ምክር አገልግሎት መስጫ መሳሪያዎችን ማጠናከር በፍትሃዊነት ላይ ያተኮረ እና የጠነከረ፣ ሚዛናዊ የሆነ እና ደህንነት ያካተተ የኮርስ እቅድ ዝግጅቶችን መፍጠር።
- ከCTE በተባበረና በተቀናጀ መልኩ ተከታታይነት ያላቸው በስራ ላይ የተመሰረቱ ትምህርት እድሎችን ለተማሪዎች በመካከለኛ እና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ደረጃ ላሉ ተማሪዎች መፍጠር።
- ለቤተሰቦች የቅድም-መዋእለ ህፃናት አገልግሎት የማግኘት እድል ማስፋፋት።
- የቀናጀ የምዝገባ ኮሜቴ የቅድም-መዋእለ ህፃናት እና የትምህርት አጋሮች ጋር በጋራ ማዘጋጀትና መምራት።
- የከተማአቀፍ የቅድም-መዋእለ ህፃናት የምልመላ ስትራቴጂ ማዘጋጀት እና በስራ ማዋል።
- ፕሮግራሞቹ እና አገልግሎቶቹ አስፈላጊ የሆኑ ፍላጎቶችን የሚያማሉ መሆኑን ለመረዳት የቅድም-መደበኛ ትምህርት ልምድ ትንተና ማድረግ እና የመዋእለ-ህፃናት የፎል ወቅት በየዓመቱ መረጃ መተንተን ።
- የቅድም-መዋእለ ህፃናት የቦታ ብዛት ለመረዳት የፕሮግራም ቀጣይነት እና/ወይም የመስፋፋት እድሎችን ለማመቻቸት ከኮሚዩኒቲ አጋሮች እና ከከተማው ጋር ትብብር ማድረግ ።
- በኮሚዩኒቲ የሚንቀሳቀሱ የቅድመ-ህፃናት እና የትምህርት ፕሮግራም ትብብር ለመቀጠል የጋራ የሙያ ትምህርትን ድጋፍ ማድረግ ።
- በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. አዲስ አንደኛ ደረጃ ሲገነባ የቅድም-መዋእለ ህፃናት አገልግሎትን ማስፋት።

ከመደበኛ ትምህርት ቤት ውጭ የሚካሄድ ትምህርት እድሎችን አስተዋፅኦ ማሻሻል።

- በመላው የዲቪዝን ደረጃ በሚካሄድ ከመደበኛ ትምህርት በኋላ ፕሮግራም አዘጋጅ ሰራተኞች የሚካሄድ የትምህርት እድሎችን አስፈላጊነት ግምገማ ጥናት ማካሄድ ።

ትምህርት የመጀመሪያ ግዜ ወደኋላ የማራዘም ተገቢነት ጥናት ማካሄድ።

- የኮሚዩኒቲ አስተያየት  በማሰባሰብ ጥናት የሚያካሂድ አማካሪ ማሰራት።

# የስትራቴጂካዊ  ሃብት ሪሶዋርስ  አመዳደብ

የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በስትራቴጂ መንገድ የተለያዩ ሪሶዋርሶችን እገዛዎችን ለት/ቤቶች እና ለዲፓርትሜንቶች ድጋፍ ያደርጋል።

የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ፕሮግራም እና ድጋፍ፤

- የገንዘብ በጀት አጠቃቀም ተገቢው አያያዝ እንዲኖረው ለማድረግ ብቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት ላይ ይውላል።
- ለጤና እና ደህንነት የተማሪዎችን አስተዋፆ ማድረግ።
- ፍትሃዊ የሆነ ውጤት ለማምጣት ተማሪዎችን ባሉበት አቅም ደረጃ ቦታ ላይ ማግኘትና ማገዝ።
- በዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ ላይ ላሉ እና ለጥቁር አሜሪካዊያን ተማሪዎች አገልግሎት የሚሰጡ የሚያስተምሩ አስተማሪዎች በተቻለ መጠን በስራቸው ላይ ለረዝም ግዜ እንዲቆዩ ለሰራተኞች ማበረታታት።

## መለኪያዎች

እኛ የእድል እና የውጤት ልዩነቶች መወገዳቸውን ለማረጋገጥ የምናሳየውን እድገት በሚከተሉት መንገዶች ክትትል እናደርጋለን፤

- በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በተማሪዎች ብዛት መጠን መሰረት ፍትሃዊነት ባለው መንገድ የገንዘብ ድጋፍ እና የሰራተኛ ምደባ ማድረግ (የሪሶዋርስ አመዳደብ ትንተና)
- ሰራተኛ በስራ የመቆየት ስሌት
- የትምህርት ቤት አውቶብስ ሰዓቱና ደህንነቱን ጠብቆ መንቀሳቀስ።
- የዋና ጽ/ቤት የተቆማትና እና ጥገና ዲፓርትሜትን ለትምህርት ቤቶች የሚያደርገው ድጋፍ ጥራት (የርእሰ መምህራን መጠይቅ)

## ስትራቴጂ  እና  የተመረጡ ተግባራት

ከፍተኛ ድጋፍ ለሚፈልጉ ሪሶዋርስ ፤ በግልፅነት ባለው መንገድ ለት/ቤቶች እና ለፕሮግራሞች መመደብ።

- የተማሪዎችን ብዛት የዋና  ጽ/ቤት ሁኔታን ጭምር ያመዛዘነ ቀመር መጠቀም።
- የፓሊሲና እና የአሰራር ለውጥ የሚያመጣ ፍትሃዊነት ላይ የሚተኩር ውይይት ማዘጋጀት ።

የበጀት ስትራቴጂ ማዘጋጀት የሚያሳድረውን ተፅእኖ እና የትምህርት አስተዳደር ዲቪዝን ወጪ በአግባቡ ለመጠቀም  ለማሻሻል።

- ከበላይ መሪዎች ጋር መስራት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን እና የወጪ ቅነሳ አማራጮችን ለመለየት።
- ለወጣው ወጪ የሚገኘውን ውጤት (ROI) አሰራር በመጠቀም ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች የመቆጣጣር ስራ ማካሄድ ወደፊት የሚሰጡ ውሳኔዎችን ለማገዝ።

ሰራተኛ በስራ የመቆየት ስሌት ማሳደግ የትምህርት ቤት ከባቢ ሁኔታ ለማሻሻል፣ የአሰራር ብቃትን ለመፍጠር እና የትምህርት አሰጣጡን ለማሻሻል።

- ይፋ የሆነ የስራ አጀማመር ሂደት እቅድ ማዘጋጀት በመጀመሪያዎች ዓመታት በስራ ላይ እገዛ ማድረግ የአመት መጨረሻ እና ከቀርብ ኋላፊዎች እና ከቆዩ ሰራተኞች ሃሳብ አስተያየት ማግኘት።

የመረጃ አያያዝ ላይ አትኩሮት በማድረግ የስራ አፈፃፀም ብቃትን ማሻሻል።

- የመረጃ አገባብን ጥራት ለማሻሻል አሰራርን ማጠናከር እና የዋና ጽ/ቤት የመረጃ አያያዝ ጥናት ማካሄድ አሁን ያለውን Munis፣Timeclock፣ Canvas፣ PowerSchool፣ እና Zimbra ጭምር በተመለከተ ማጥናት።

ደህንነቱ የተጠበቀ ዘመናዊ እና ምቹ ተቆማት እና አውቶብሶችን ለተማሪዎች እና ለሰራተኞች ማዘጋጀት።

- ትምህርት ቤቶች ዘመናዊ የማድረግ ስራ መቀጠል አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ በመካከለኛ እና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ።
- በኦዲት በየተለዪ ግዜው መሰረት የDivision's ተቆማት እቅዶችን አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ።
- የትምህርት ቤት አውቶብስ ሰዓቱና ደህንነቱን ጠብቆ መንቀሳቀስ መቻሉን በሚመለከት ግምገማ ማካሄድ ።

ቢያንስ ለግዢ ፣ ለጥገና እና የቴክኒዋሎጂ ቅንጅትን፣ ለህንፃዎች አቅም ግንባታ በሙያ ትምህርት አጠቃቀም የሚሆን የገንዘብ በጀት ማድረግ።

- የተማሪዎች እና የሰራተኞች መሳሪያዎችን እና አስፈላጊ የኔትወርክ መሰረታዊ አገልግሎት መስጫ መሳሪያዎችን በየሶስት ዓመት የመተካት የአሰራር ሂደት መፍጠር።
- ተማሪዎችን ማእከል ያደረገ ሞዴሎችን፣ የፈጠራ ማስተማሪያ ልምዶችን እና በቴክኒዋሎጂ በመጠቀም የሙያ ማሻሻያ ለውጦችን ለሚኪያሂዱ የሙያ ትምህርት እድሎችን ለሰራተኞች ማዘጋጀት።

አስተማማኝ፣ ሊያድግ የሚችል እና ግልፅነት ያለው የትምህርት አስተዳደር ስራዎችን እገዛ የሚያደርግ እና የተሻለ አገልግሎት እና ፍትሃዊነት እንዲኖር የሚያስችል የቴክኒዋሎጂ መሰረተልማት ማቅረብ።

- ፍትሃዊነት በተሞላበት መልኩ የኮምፒወተር አቅርቦት ማከናወን (ክሮምቡክ፣ ላፕቶፕ፣ መግለጫዎችን ለማቅረብ የሚያስችሉ የተለያዩ መሳሪያዎች፣ ወዘተ..) በዲቪዝኑ በሙሉ ላሉ ተማሪዎችና ለሰራተኞች ማቅረብ።
- የቴሌኮምንኬሽን ኔትዋርክ ግንኙነት ድጋፍ እና የኔትወርክ መገልገያ መሳሪያዎች ጥገና ማድረግ።
- አንድ ወጥነት ያለው የትምህርት አሰጣጥ ስራውን እና የቢሮ ውስጥ ስራውን ለማካሄድ የሚያስችል በትምህርት አስተዳደር ዲቪዝኑን በሙሉ ለሚያገለግል የሶፍትዌር/ አፕልኬሽን ማዘጋጀት።
- አንድ ወጥነት ያለው ከተማሪዎች፣ ሰራተኞች፣ ቤተሰቦችና ከህብረተሰቡ ጋር የመረጃ ልውውጥና ግንኙነት ለማመቻቸት የሚያስችል የዲጅታል መሳሪያዎችን ማዘጋጀት።
- አገልግሎት ማግኘት በሚፈልገበት የስራ ቦታዎች የኢንተርኔት ግንኙነት እና ከስራ ቦታዎች ውጭ የኢንተርኔት አገልግሎት እንደአስፋላጊነቱ ተማሪዎች ማግኘት እንዲችሉ ማስቻል።

# የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ፤

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሁሉም ቤተሰቦች እና የኮሚዮኒቲ አባላት መልካም አቀባበል መኖሩ እንዲሰማቸው፣የተከበሩ እና ዋጋ የተሰጣቸው መሆኑ እንዲሰማቸው አስፈላጊውን ያረጋጋጣል።

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ቤተሰቦች እና የኮሚዪኒቲው ተሳትፎ፤

- በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት እንዲካተቱ ማድረግ።
- የትምህርት አሰጣጥ ሂደቱ እንዲካሄድ እና አገልግሎት ለተማሪዎች እንዲያገኙ አቅም እንዲኖራቸው ማስቻል።
- ከአጋር ድርጅቶች ጋር የተቀናጀ  የአገልግሎት አሰራር መኖሩን ማረጋገጥ።

## መለኪያዎች

እኛ የእድል እና የውጤት ልዩነቶች መወገዳቸውን ለማረጋገጥ የምናሳየውን እድገት በሚከተሉት መንገዶች ክትትል እናደርጋለን፤

- ለልጆቻቸው ውጤታማነት አጋር የሆኑት በትምህርት ቤቶች አቀባበል መልካም ስሜት፣ መከበራቸው እና አቅም የሰጣቸው መሆኑ የሚሰማቸው የቤተሰብ ብዛት በመቶኛ ፐርሰንት(መጠይቅ)
- በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ሃሳባቸው የተካተተ እና ዋጋ የሚሰጠው መሆኑ የሚሰማቸው ቤተሰቦች ብዛት በመቶኛ ፐረንሰንት (መጠይቅ)
- በትምህርት ቤቶች አቀባበል መልካም ስሜት፣ መከበራቸው የተሰማቸው መሆኑን እና ለተማሪዎች የትምህርት እና የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱን በማገዝ አቅም የሰጣቸው መሆኑ የሚገልፁ የበጎ ፍቃደኞች ብዛት በመቶኛ ፐርሰንት (መጠይቅ)

(ሁሉም መጠይቆች ወካይ የሆነ ድምፅ በሁሉም ቡድኖች ማሳየት ይኖርባቸዋል።)

## ስትራቴጂዎች እና የተመረጡ ተግባራት

ቤተሰብን ማሳተፍ - በተለይ ስደተኞች እና የጥቁር አሜሪካዊያንን ቤተሰቦች - በልጆቻቸው የትምህርት  እና በትምህርት ቤቶች እና በአስተዳደር ዲቪዝን የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት።

- የቤተሰብና የማህበረሰብ ተሳትፎ የተግባር እቅድ በስራ ማዋል።  ሁሉም ቤተሰቦች በልጆቻቸው የትምህርት ጉዳይ ላይ እንደ እኩል አጋር የሚሳተፉ፣ መልካም አቀባበል  እና የተደገፉ መሆኑ እንዲሰማቸው ማድረግ።
- በቤት ውስጥ የሚናገሩት ቋንቋ ሳይገድባቸው ወላጆች የተማሪዎች ትምህርት የሚጠበቅባቸውን ጉዳዩች ምን እንደሆኑ እንዲረዱ ማድረግ፣ የተማሪዎቻቸው ውጤታማነት እንዴት መደገፍ እንደሚችሉ እና ለእገዛ የት መሄድ እንደሚችሉ ማስረዳት።
- መደበኛ የሆነ የኮሚዩኒቲ ዝግጅት በመላው የትምህርት ቤት ዲቪዝኑ ትምህርት ቤቶች ማካሄድ፣ ቤተሰቦች ትርጉም ባለው መንገድ እንዲሳተፉ ለማድረግ ከቤተሰቦችና የቤተሰብና የማህበረሰብ ተሳትፎ ቡድን እና ከወላጆች አገናኝ ጋር አብሮ መስራት ።
- በምርምር ላይ የተመሰረተ ስትራቴጂ በማዘጋጀት የተማሪዎችን ማህበራዊ ስሜት እና የአካዳሚ ደህንነት ለማስጠበቅ እውነተኛ፣ ቀጣይነት ያለው ግንኙነት ከቤተሰቦች ጋር በመፍጠር ።
- ከአንድ በላይ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሰራተኞች ቁጥር  በትምህርት ቤቶች  እንደአስፈላጊነቱ መጨመር የተማሪዎችን ቁጥር ባዛት ለመወከል።
- የባህል እውቀት እና እንግዳ የማስተናገድ ስልጠና ሰራተኞች፣ አስተማሪዎች እና የአስተዳደር ኋላፊዎች እንዲያገኙ ማድረግ።

የተማሪዎች እና የቤተሰቦችን የጤና፣ የማህበራዊ ጉዳይ አገልግሎት እና የአካዳሚ ፍላጎቶችን ለማሞላት ከከተማው እና ትርፋማ ካልሆኑ አጋር ድርጅቶች ጋር መስራት።

- በጋራ የእቅድ ዝግጅት ሂደት ተሳትፎ ካላቸው ከከተማ ተቋማት ጋር ቁልፍ የጋራ ፍላጎት በሚታይባቸው ጉዳዬች ላይ የተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው የጤና እና የአእምሮ ጤና በተመለከተ ትብብር መቀጠል።
- ከከተማው እና ትርፋማ ካልሆኑ አጋር ድርጅቶች አብሮ መስራት፣ፍላጎትን ለማሞላት በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የኮሚዩኒቲ ፍላጎት ትንተና ማካሄድ።
- ከፍተኛ ፍላጎት በሚያሳዩ ትምህርት ቤቶች የተሞላ ድጋፍ ለተማሪዎች እና ቤተሰቦች መስጠት።

ትምህርት ቤቱ የሚደግፉ የኮሚዩኒቲ በጎ ፈቃደኞችን ውጤታማነቱን እና ስብጥር ማሳደግ።

- ለትርፍ የማይሰሩ ድርጅቶችና በጎ ፍቃደኞች የስራ ድርሻ ግልፅ የሆነ አሰራር መመሪያዎችን ለመፍጠር ከትምህርት ቤቶች ጋር መስራት።
- ከወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎ ቡድን ጋር መስራት በትምህርት ቤት ተሳትፎ የሚያደርጉ የበጎ ፍቃደኞችን ስብጥር ለማሳደግ እና በስራ ለተሰማሩ ወላጆች እንቅፋቶችን ለመቀነስ።

ለተማሪዎችን እድሎችን ለማስፋት የንግድ ተቆማት አጋሮች ማስፋፋት።

- በዚህ በሰሜን ቨርጅኒያ የቴክኒዋሎጂ ማእከላት እድሎች ለማስፋፋት ለመጠቀም የሚያስችል እቅድ ማውጣት።
- ለተማሪዎች የስራ የሙያ መስክ ምርጫ የሚመርጡበትን እድል እንዲኖራቸው አንድ አሰራር መፍጠር።

# የስትራቴጂክ እቅድ የቃላት ትርጎሜ

የውጤት ልዩነት**(Achievement Gap)** ፣ በትምህርት መስክ የውጤት ልዩነት(Achievement Gap) የሚለው ቃል የሚገልፀው በተማሪ ቡድኖች መካከል የሚታየው የአካዳሚ ውጤት ልዩነት ነው። ውጤታማነት ከሚለኩበት መስፈርቶች መካከል የውጤት ልዩነት የሚያሳየው፤ የክፍል ደረጃ፣ መደበኛ የመመዘኛ ፈተና ውጤት፣ በኮርስ ምርጫ፣ ትምህርት የሚያቋርጡ ብዛት እና ኮሌጅ የሚያጠናቅቁ ብዛት ላይ ይታያል።

የጥቅም ብልጫ /ተጠቃሚነት እድሎች፤ የተያያዙ ሁኔታዋች ወይም የተወሰነ ስብስብ ሰዎች ቡድን ሌሎች በተለምዶ ከሚያገኙት በበለጠ በየቀኑ ተጠቃሚ መሆን። አንድ ሰው መኖሩንም ሳያውቅ የጥቅም ብልጫ ሊኖር ይችላል።

ዋና እምነቶች፤ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. መሰረታዊ እምነት። ይህ መመሪያ የእንቅስቃሴ ባህሪን አቅጣጫ የሚያሲዝ ይሆናል እናም ሰዎች በትምህርት አስተዳደር ዲቪዝኑ ስም ውሳኔ በሚሰጡበት ወቅት እገዛ ያደርጋል።

የእድገት ደጋፊ ገፅታዎች አቀራረብ፤ እነዚህ 40 ቀና መልካም ድጋፎች እና ጥንካሬዎች ልጆች እና ወጣቶች ለማደግ እንደ እድገት መሰረት ይሆኖቸዋል። ተማራማሪዎች እንዳለመለከቱት እነዚህ ጠቃሚ ገፅታዎች በወጣት ህይወት ላይ መልካም የሆነ ተፅእኖ ይኖራቸዋል።

የፍትሃዊነት ውጤት፤ በኮሚዩኒቲ እንዲኖር፣ እንዲሰፍን አላማነት የምናስቀምጣቸው ሁኔታዋች።

የትምህርት ፍትሃዊነት፤ በዘር፣ በኢኮኖሚ እና በሌላ መስክ ባሉ ልዮነቶች ምክንያት የሚኖረው የትምህርት ልዮነት እንዲቀንስ እና እንዲወገድ ማድረግ ። ጥሩ የትምህርት ውጤቶች በፍትሃዊነት በተመጣጣነ መልኩ በሁሉም የህዝብ አካል እና በተለያዮ ቡድኖች መዳረስ ይኖርበታል። ጥሩ ያልሆኑ አሉታዊ ውጤቶች እና ተመጣጣኝ ያልሆኑ ሁኔታዎች ለሁሉም ቡድኖች አካሎች እንዲቀንሱ ማድረግ።

የትምህርት ጥራት፤ በምናደርጋቸው ስራዎች ሁሉ ደረጃውን ከፍ እናደርጋለን። ተማሪዎች ለህይወት የተዘጋጁ እና የሚያገናዝቡ ዜጎች እንዲሆኑ እናስተምራለን። ተማሪዎችን እና ሰራተኞች ማንነታቸው እና ባህላቸውን እንዲጠብቁ ድጋፍ እናደርጋለን። ትእዛዝ ተከታይ እና ከፈተና ውጤት ይልቅ ቁም ነገር ያለው ይዘት፣ ጥልቀት እና የጠለቀ ሃሳብን መፍጠር በጣም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው ።

ግቦች፤ የትምህርት ቤት አስተዳደር ፍትሃዊነት ለማረጋገጥ የሚያግዙ አምስት ጉዳዮችን የያዘ አቀራረብ፣ የዲቪዝኑን ስራዎች ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቶች (KPIs) ማሞላታቸውን ለመመልከት እና ዲቪዝኑን የእድገት ለውጦችን ክትትል ለማደረግ ያስችላሉ። እያንዳንዱ ግብ እንዴት የተፈላጊ የሆኑ ግቦችን አፈፃፀም የሚወስኑ መስፈርቶችን ይይዛል። እያንዳንዱ ግብ በተጨማሪ እንዴት ግቡ ላይ መድረስ እንደሚቻል የሚያሳዩ ብዙ ስትራቴጂዎች እና የተመረጡ ተግባራትን ይይዛል።

የተመረጡ ተግባራት፤ በእያንዳንዱ ስትራቴጂ እነዚህ ቅድሚያ ያላቸው ፕሮጀክቶች መከናወን ያለባቸውን ተግባራት መለካት የሚችሉ ግቦችን አፈፃፀም ይገልፃሉ። እነዚህ የተመረጡ ተግባራት ከትምህርት ቤት እና የአስተዳደሩ የማሻሻያ እቅድ ጋር እንዲስማሙ የተደረገ ሲሆን የአፈፃፀም ሂደቶችን እና መለኪያ መስፈርቶችን ለይተው ያስቀምጣሉ።

ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቶች **(KPIs)**፤ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሊያሳካ የሚያስበውን አጠቃላይ የተማሪ አፈፃፀም ውጤቶች እና የትምህርት ቤት አስተዳደሩ የመጨረሻ ውጤታማነት ለመገምገም በአገልግሎት ላይ ይውላል።

መለኪያዎች ፤ የትኞቹ ግቦች ምን ያህል ተፈፃሚነት እንዳላቸው ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የሚወስንባቸው መንገዶች ናቸው።

ተልእኮ፤ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. መሰረታዊ አላማ በትምህርት ቤት አስተዳደር ውስጥ ላሉ እና ለህዝብም ጭምር የተዘጋጀ አጭር መግለጫ ነው። "ለምን እኛ ተፈጠርን?" የሚለውን መልስ ይሰጣል።

እድል የማግኘት ክፍተት፤ ለአካዳሚ ውጤታማነት ለምሳሌ ቅድሚያ የህፃናት የልጆች ትምህርት እና/ወይም ጠንካራ፣ አሳታፊ እና ተገቢነት ያለው ጥራት ያለው ትምህርት እድል እና እገዛ ሪሶዋርስ ለማግኘት ያለው ክፍተት ።

የዘር ፍትሃዊነት፤ ዘር የአንድን ሰው ህይወት፣ እድል ማግኘት እና ውጤት የማይወስነው መሆን ሲረጋገጥ።

ዘዴዎች ስትራቴጂዎች ፤ የትምህርት አስተዳደር እቅድ እያንዳንዱን ዓላማ እንዴት እንደሚያሳካ የሚያመለክቱ ከፍተኛ ደረጃ ተግባራት። በእያንዳንዱ በተለዩ ስትራቴጂዎች የተመረጡ ተግባራት፤ እያንዳንዱ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ፕሮጀክቶች የክንውኖች ስኬት መለካት የሚያስችሉ።

የተግባር መርሕ፣ በተማሪው ውጤታማነት ትልቅ ለውጥ ለማምጣት እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ተማሪዎች፣ ጥቁር እና ስፓኒሽ አሜሪካዊያን ተማሪዎች) የእንግሊዘኛ ቋንቋ (EL) እና የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች የእድል እና የውጤት ልዩነት ለማጥፋት ምን ተግባራት መከናወን እንዳለባቸው የሚያሳይ መሰረታዊ እምነት። የተግባር መርሁ የትምህርት ቤት አስተዳደሩ እይታውን ለማሳካት፣ ተልእኮውን ለመፈፀም እና ዋና እምነቶችን ማክበሩን ያረጋግጣል።

ባለፉት አሰቸጋሪ ህይወት ላይ የተመሰረተ **(Trauma-Informed)**፤ የቀድሞ ከባድ የልጅነት ህይወት ልምድ (ACES) የጎላ እውቅና ማግኘት ባለፈው ልምድ ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ኮሚዩኒቲ ይፈጥራል።

እይታ፤ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ወደፊት ምን ለማግኘት እንደሚሞክር የሚያሳይ ግልፅ የሆነ ሃሳብ።

# የጋራ የእቅድ ዝግጅት ሂደት

አሌክሳንደሪያ ተቆርቋሪ፣ የሚገነዘብ እና ኮሚዩኒቲ አሳታፊ በመሆኑ በራሱ ማንነት ይኮራል - እዚህ ኖሪ ለሆኑ አገልግሎት እና ለአጠቃላይ ለህዝብ ጥቅም ፍላጎት ለማሟላት በትብብር ይሰራል። የአሌክሳንደሪያ ዜጎች ራሳቸውን በግል እንዲሁም የጋራ ህብረት አንድ አካል በመሆን በከተማው ኖሪ የሆኑትን የሌሎችን ህይወት ለመለወጥ ያላቸውን ፍላጎት ይገልፃሉ።

በ2019 የከተማ ሶስት ዋና ከከተማው ጋር የተሳሳሩ ዋና እቅዶች የመከለሻ ግዜ ሲገጣጠም አንድ "ጥሩ አጋጣሚ" ተከሰተ - የአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤት ስትራቴጂክ እቅድ፣ የአሌክሳንደሪያ የኮሚዩኒቲ እና የሰብአዊ አገልግሎቶች ዲፓርሜንት የልጆችና የወጣቶች ዋና ቁልፍ እቅድ (CYMP)፣ የአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት ጤናማ አሌክሳንደሪያ ትብብር የአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት የማሻሻያ (CHIP) እቅዶች ክለሳ የሚደረጉበት ወቅት በመገጣጠሙ። እነዚህ ተቋማት በስፐሪን 2019 የጋራ እቅድ አዘጋጅ ቡድን አቋቁመው ለእቅዶቻቸውን ተጨማሪ ጠቀሜታ የሚያስገኝ በጋራ ኮሚዩኒቲውን የሚያሳትፍ እድል በመፍጠር፣ በጣም ጠቃሚ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እና በጋራ በሚገኙ ውጤቶች ላይ በማተኮር እቅዶቻቸውን በጋራ ለማዘጋጀት ተስማሙ ።

ተለያይቶ ከመስራት ይልቅ በጋራ የመስራት ውጤት ለአሌክሳንደሪያ በሙሉ ጠቀሜታ እንዳለው ታይቶል  እና  በኮሚዩኒቲው ለወደፊቱ ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በሞዴልነት ያገለግላል።

በዚህ ሰነድ ውስጥ የተካተቱትን የዚህ የጋራ የእቅድ ዝግጅት እንቅስቃሴን ውጤት እና ሌሎች በዚህ የጋራ እንቅስቃሴው የተከናወኑትን እንዲመለከቱ እንጋብዛለን።

እነዚህን እቅዶች ማዘጋጀቱ ጠቃሚ ቢሆንም በአግባቡ ውጤታማ በሆነ መልኩ በስራ ማዋል የበለጠ አስፈላጊ ጉዳይ ይሆናል።  በዚህ መሰረት የጋራ የእቅድ ዝግጅት ቡድኑ ወደ የጋራ አስፈፀሚ ቡድን እንዲለወጥ ይደረጋል  እቅዱን በስራ የማዋል በዚህ የአፈፃፀም ሂደት የተፈጠረውን ትብብር ለመቀጠል፣ በቀጣዪ አምስት ዓመታት እና የተግባር መዋሃድን ለማረጋጋጥ፣ የተቀናጀ የኮሚዩኒቲ ተሳትፎ ፣ የመረጃ አጠቃቀም እና በሚቻልበት ወቅት የጋራ ሪሶዋርስ ለመጠቀም።

# የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ 2025 ስትራቴጂክ እቅድ ዝግጅት ኮሜቴ አባላት፤

Ruba Afzal
Leslie Alexander
Mignon Anthony
Naeem Baig
David Baker
Ana Bonilla
Caitlin Bousquet
Gwen Bridges
Shawn Brown
Hannah Brownell
Eden Buba
Andaiye Cammon
Dr. Julie A. Crawford
William Deeker
Gaynelle Diaz
Caroline Doughty
Chelsea Eickert
Danielle Esposito
Mariam Fikre
Katrina Ford
Leah Fraley
Mary Gaddis*
Ramee Gentry*
Alejandro Gomez
Jacinta Greene*
Robert Gunby
Dr. Stacey Hardy-Chandler*
Christopher Harris
Dr. Elizabeth Hoover

የምክር አገልግሎት የተሰጠው ሰጪ ፡
FourPoint Education Partners

Kurt Huffman
Dr. Gregory C. Hutchings, Jr.*
Stephen Ingram
Michelle Italiaander
Kobe Jackson
Amanda Kelley
Megan Langley
Janelle Lee
Dr. Bethany Letiecq
Helen Lloyd
Joanna Lovo
Abigail Lower
Laurie MacNamara
Dr. Gerald R. Mann, Jr.
Dr. Victor Martin
Sean McEnearney*
Sofia Melendez-Contreras
K. Nicholas Miller
Pedro Morales*
Ingris Moran
Dr. Terri Mozingo
Marie Muscella
Dr. Bethany Nickerson
Shanel Norwood
Andrew Orndorff
Aisha Ortiz
Clinton Page
David Paladin-Fernandez
Matthew Parrish

Rene Paschal
Dr. Lisa Piehota
Jane Richardson
Patricia Rodgers
Ruth Santos*
Matthew Schilling
RaAlim Shabazz*
Matthew Stensrud
Natalie Talis
Veronica Tellez*
Ewan Thompson*
Brent Trigg
Dominic Turner
Lauren Vitello
Terry Werner
Dr. Stephen M. Wilkins
Terry Wright
Sharon Yandian

*የአደራጅ ኮሚቴ አባላት

ዋና የእቅድ ዝግጅት ቡድን አባላት፤

Alejandra Caballero
Christina Constantine
Nathan Goldstein
Cheryl Robinson
Dr. Jennifer Whitson
Kennetra Wood

# ከኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ጋር ለመገናኘት፤

ተጨማሪ እና ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት 2025 ስትራቴጂክ እቅድ ድረገፅ፤ **www.acps.k12.va.us/2025**

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በቲዊተር፤ በፌስቡክ እና ኢንስታግራም ይከታተሉ። **@ACPSk12**

የትምህርት ቤቶችን ማህበራዊ ሚዲያ ይከታተሉ፤ **www.acps.k12.va.us/socialmedia**

የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ኤክስፕረስ፣ የትምህርት ቤት መድሔቶችን እና የድንገተኛ ጉዳዩች ማስታወቂያ መረጃዋችን ለማግኘት ይመዝገቡ፤
**www.acps.k12.va.us/lists**

## ይህ እቅድ የተዘጋጀው እና የፀደቀው በጁን **2020** በሚከተሉት አመራር ሰጪነት ነው፤


### የኤሌክሳንደሪያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ

ዲስትሪክት **A**

Jacinta Greene

Michelle Rief

Christopher A. Suarez

ዲስትሪክት **B**

Cindy M. Anderson (ሊቀመንበር)

Margaret Lorber

Veronica R. Nolan

(ም/ ሊቀመንበር)

ዲስትሪክት **C**

Meagan L. Alderton

Ramee A. Gentry

Heather Thornton


### የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንቴንደንት (ዋና ስራ አስኪያጅ)

ዶ/ር ግሪጎሪ ሲ. ሐትቺንግስ ( Gregory C. Hutchings, Jr).


የአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች
1340 Braddock Place • Alexandria, VA 22314 • 703-619-8000 • www.acps.k12.va.us